# የአብክመ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

# የ2002 በጀት ዓመት <u>ዓመታዊ</u> ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

ሐምሌ 2002 ዓ.ም
ባህርዳር

# ማውጫ

ማጠቃለያ ----------------------------------------------------------------------------------------------3
የዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም............................................................................................................4
1. መከላከል.......................................................................................................................................4
1.1. የመረጃና ትምህርት ስርፀት ..........................................................................................................4
1.1.1. የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት......................................................................................................4
1.1.2. የመረጃ ትምህርትና ስርፀት ቁሳቁስ ...........................................................................................5
1.1.3 የኤድስ መረጃ ማዕከላት................................................................................................................7
1.2. የማህበረሰብ ውይይት .....................................................................................................................7
1.3 የማህበረሰብ አቀፍ ኤድስ ፕሮግራም ..............................................................................................10
1.4 የኤች.አይ.ቪ. የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት.........................................................................11
1.5 ኤች አይ ቪ. ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል .................................................................13
1.6 የኮንዶም ትውውቅና ሥርጭት .......................................................................................................15
1.7 የአባላዘር በሽታዎችን መከላከልና ማከም ..........................................................................................17
1.8 በስራ ቦታዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መከላከል .................................................................................18
1.9 ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የተከናወኑ ተግባራት..................................18
2. ድጋፍና ክብካቤ...........................................................................................................................20
*2.1. ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝባቸውና ለኤድስ ሀሙማን ድጋፍና የማህበራት እንቅስቃሴ*........20
*2.2. ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ልጆች የሚደረግ ድጋፍ*...................................................................23
2.3 ለተጋላጭ ወጣቶች ሴቶች የገቢ ማስገኛ ስልጠናና ድጋፍ.................................................................25
2.4 የፀረ ኤች አይ ቪ. መድሃኒት አገልግሎት .........................................................................................25
3. የአቅም ግንባታ.............................................................................................................................27
3.1 ስልጠናዎች ..................................................................................................................................27
3.2 የጤና አገልግሎት መስጫ ተkማትን ማስፋፋት.................................................................................30
3.3 በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መረጃ የሚሰጡ ማዕከላትን ማከምና ማጠናከር ...................................................30
3.4 የኤችአይቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ አፈፃፀም ..................................................................................31
3.5 በየደረጃው ያሉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ማ/ጽ/ቤቶችን አቅም ማጠናከር .................................................31
4. የክትትልና ድጋፍ ተግባራት ........................................................................................................31
5. የበጀት አጠቃቀምና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ......................................................................................33
6. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች ...........................................................40
6.1 ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች..............................................................................................................40
*6.2 የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች*.....................................................................................................40
6.3 የታዩ መልካም የስራ እቅስቃሴዎች...................................................................................................41
7. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች .................................................................................................................42

# ማጠቃለያ

በ2002 ባጀት አመት በክልሉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት ለመግታት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ህብረተሰቡ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በባለቤትነትና በግንባር ቀደምነት እንዲሰለፍ እየተደረገ ነው፡፡

በዚህም መሠረት በ2002 ባጀት አመት፤

- 14278189 የህብረተሰብ ክፍሎች በልዩ ልዩ መንገዶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት አግኝተዋል፣
- 3523277 የመረጃ ትምህርትና ህትመት ቁሳቁሶች ተሰራጭተዋል
- 3120732 ሰዎች የኤች.አይ.ቪ. የምርና የደም ምርመራ አድርገዋል
- 201291 ነፍሰ ጡር እናቶች ኤች.አይ.ቪ. ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ የመከላከል አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡
- 17930 አዋቂ ሰዎችና 2002 ህፃናትን በአዲስ መልኩ የፀረ ኤች አይ ቪ. መድሃኒት እንዲጀምሩ ተደር¹ል፡፡
- 18864321 የወንድና 142867 የሴት ኮንዶም ተሰራጭቷል
- በክልሉ በሚገኙ 3409 ቀበሌዎች በ 8876 የማህበረሰብ ውይይት ጣቢያዎች እና በ1846 ት/ቤቶች በድምሩ በ8720 ጣቢያዎች የማህበረሰብ ውይይት ይካሄዳል፡፡
- በ 3287 ቀበሌዎች የማህበረሰብ አቀፍ ፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራም በማካሄድ 1880912 ቤተሰቦች መድረስ ተችሎል፡፡
- 3323 መ/ቤቶች/ተkማት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ማስፈፀሚያ በጀት መድበዋል፡፡
- 2701 መ/ቤቶች/ተkማት የኤድስ ፈንድ አkቁመዋል፡፡
- 144217 ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ያለባቸው ወገኖች የተለያዮ ድጋፍና ክብካቤ አግኝተዋል፡፡
- 264209 ወላጆቻቸውን በሞት ላጡ ህፃናት ድጋፍና ክብካቤ ተደርጓል፡፡
- 151556 ሰዎች የአቅም ማሳደጊያ የተለያዩ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡
- 22,5521,334.68 በበጀት ዓመቱ ከፕሮጀክት ለስራ ዝግጁ የነበረ ሲሆን 17,6452,246.08/78.82%/ ስራ ላይ ዉሎ ተወራርዷል፡፡

# የዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም

## 1. መከላከል

በ2002 በጀት አመት በዕቅድ ተይዘው በተለያዩ አካላት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የኤች.አይ.ቪን ስርጭት የመከላከል ሥራ አንዱና ዋነኛዉ ነው፡፡ ሕብረተሰቡም የኤች.አይ.ቪ የምክርና የደም የምርመራ፣ ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል፣ የፀረ ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ተጠቃሚነትና የህክምና ባህሉን በማሳደግ በተለይም ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የበለጠ የሚያጋልጡ የአባላዘር በሽታዎችን ፈጥኖ የመታከም አገልግሎቶች ተጠቃሚ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም በኮንዶም አጠቃቀምና በሌሎችንም በርካታ መሻሻሎች ተገኝተዋል፡፡ በዚህም መሠረት በበጀት ዓመቱ በመከላከሉ  የነበረው ክንውን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1.1. የመረጃና ትምህርት ስርፀት

#### 1.1.1. የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት

ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ስለበሽታው ምንነት፣ መተላለፊያና መከላከያ ዘዴዎች እንዲሁም ስለሚያደርሰው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጫና ለሕብረተሰቡ የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት በየጊዜዉ በተለያዩ መንገዶች እየተሰጠ ይገኛል፡፡

በ2002 የበጀት ዓመት  የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለ 14278189 ሕዝብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሠጥቷል፡፡ የዕቅድ ክንውኑም 130%፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቱ በገጽ ለገጽ ገለፃ ዝግጅቶች፣ በሚነበቡ ቁሳቁሶችና በሚደመጡ መረጃዎች (ሚዲያ)፣ በስነ ጽሑፍ፣ በድራማና በግጥም፣ በአቻ ለአቻ ውይይት፣ በሚኒሚድያ፣ በማህበረሰብ ውይይት፣ በፓናል ውይይት፣ ኤች.አይ.ቪ በደማቸዉ ውስጥ ያለባቸው ሠዎች በሚሰጡት የምስክርነት ቃል፤ በእምነት ተቋማት፣ በት/ቤቶች፣ በገበያ ቦታዎችና በስብሰባ ቦታዎች ላይ ግንዛቤው እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡

በሐይማኖታዊና ህዝባዊ በዓላት ቀን ወቅታዊ መልዕክቶች እንዲተላለፉ ከተለያዩ አካላት ጋር በመሆን እንቅስቃሴ በማድረግ የአፈፃፀም መሻሻል እንዲኖር ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በክልሉ ውስጥ የሚደረጉትን እንቅስቃሴዎች በሬዲዮ፣በቴሌቪዥን በጋዜጣ፣በኤፍኤምና በዜና ፕሮግራሞች በብዙሃን መገናኛ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በ2002 በጀት ዓመት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት በዞን ደረጃ

| ተ.ቁ | ዞን/ክልል | መለኪያ | የ2002 በጀት ዓመት ዓመታዊ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | % |
| 1 | ደቡብ ወሎ | ቁጥር | 960165 | 1824575 | ***190*** |
| 2 | ሰ/ሸዋ | » | 919545 | ***1264595*** | ***137*** |
| 3 | ምስራቅ ጎጃም | » | 1208141 | 1714824 | 141 |
| 4 | አዊ | » | 1078328 | ***1390761*** | ***128*** |
| 5 | ምዕራብ ጎጃም | » | 2000000 | ***2619731*** | ***130*** |
| 6 | ሰ/ጎንደር | » | 2535630 | 2521451 | 99 |
| 7 | ደቡብ ጎንደር | » | 892000 | ***1108180*** | ***124*** |
| 8 | ሰ/ወሎ | » | 224140 | ***502125*** | ***224*** |
| 9 | ዋግ ኽምራ | » | 570980 | 642176 | 112 |
| 10 | ኦሮሚያ | » | 465320 | **470770** | **101** |
| 11 | ባህር ዳር | » | 200000 | **136001** | **68** |
| 12 | ክልል | » | | **83000** | |
| | ድምር | | **11054249** | ***14278189*** | ***130*** |

## 1.1.2. የመረጃ ትምህርትና ስርፀት ቁሳቁስ ስርጭት

በተለያዩ የመረጃና ትምህርት ቁሳቁስ አማካኝነት ለሕብረተሰቡ ትምህርት መስጠት የባሕሪ ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል ለመቆጣጠር ድጋፍ፣ እንክብካቤና የህክምና አገልግሎት ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ቁልፍ ሚና አለው::

በተለያዩ አካላት ተዘጋጅተው ለሕብረተሰቡ የሚሠራጩት የመረጃ ትምህርትና ስርፀት ቁሳቁሶች የህብረተሰቡን ደረጃ ያገናዘቡ ናቸው:: በዚህ መሠረት በበጀት ዓመቱ ከተሰራጩት የመረጃና ትምህርት ቁሳቁሶች መካከል በራሪ ጹሑፎች፣ ብሮሸሮች፣ ፖስተርና የመሳሰሉት ይገኙበታል:: በክልልና በዞኖች በድምሩ 3,523,277 የተለያዩ የመረጃና ትምህርት ቁሳቁስ ስርጭት ተካሂዷል:: ይህም የዕቅዱን 180% አፈፃፀም ያሳያል::

## የመረጃና ትምህርት ቁሳቀስ (ህትመቶች) ስርጭት በዓይነት

| ተቁ | ዞን /ወረዳ | መለኪያ | ዓመታዊ ዕቅድ | ክንውን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በራሪ ፅሁፍ | ብሮሸር | ፖስተር | መጽሔት | ካኔቴራና ኮፍያ | ሌሎች ህትመቶች | ድምር | % |
| 1 | ደቡብ ወሎ | ቁጥር | 185040 | 82841 | 30707 | 7788 | 8095 | 8712 | 14687 | 155830 | 84 |
| 2 | ሰ/ሸዋ | » | 360000 | 305633 | 15754 | 8469 | 3411 | 3518 | 63422 | 400207 | 111 |
| 3 | ምስራቅ ጎጃም | » | 229766 | 132714 | 11277 | 3997 | 1256 | 1019 | 24715 | 174853 | 76 |
| 4 | አዊ | » | 100000 | 57173 | 5055 | 626 | 1284 | 336 | 5730 | 70204 | 70 |
| 5 | ምዕራብ ጎጃም | » | 191200 | 101994 | 17562 | 4728 | 2950 | 1129 | 1076 | 137586 | 71 |
| 6 | ሰ/ጎንደር | » | 326731 | 258524 | 45952 | 14768 | 1898 | 1774 | 7390 | 330306 | 101 |
| 7 | ደቡብ ጎንደር | » | 481060 | 1039492 | 62736 | 14352 | 3139 | 3400 | 10220 | 1133339 | 235 |
| 8 | ሰ/ወሎ | » | 76480 | 44290 | 10564 | 1066 | 481 | 1088 | 20868 | 78357 | 102 |
| 9 | ዋግ ኽምራ | » | 10800 | 25381 | 5084 | 1348 | 2739 | 848 | 878 | 36278 | 335 |
| 10 | ኦሮሚያ | » | 40000 | 32382 | 29023 | 3070 | 1597 | 1379 | 8414 | 75865 | 189 |
| 11 | ባ/ዳር ከ/አስ. | » | 13564 | 15965 | 17542 | 531 | 953 | 563 | 387 | 35941 | 264 |
| | ክልል | | | 157892 | 311352 | 17896 | 52250 | 120 | 366023 | 894511 | |
| | ድምር | | 2014641 | 2254281 | 562608 | 78639 | 80053 | 23886 | 512788 | 3523277 | *180* |

### 1.1.3 የኤድስ መረጃ ማዕከላት

በአማራ ክልል ውስጥ ከብሔራዊ የኤድስ መረጃ ማዕከል ጋር በመተባበር በባህር ዳር፣ በደሴ፣ እና በጎንደር ከተሞች የኤድስ መረጃ ማዕከላት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

ማዕከላቱ በዋናነት ህብረተሰቡ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ተዛማጅ ጉዳዮች ጠቃሚ መረጃ በኢንተርኔት፣ በኦዲዮ ቪዥዋልና የህትመት ውጤቶች በማግኘት ግንዛቤውን እንዲያሳድግ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በተጨማሪም በመስኩ የሚደረጉ ጥናቶችን በማገዝ አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ።

በክልሉ የሚገኙት ሦስት የኤድስ መረጃ ማዕከላት በበጀት ዓመቱ ተጠቃሚዎችን በተዘረዘሩት አገልግሎቶች ያስተናገዱ ሲሆን 32709 ወንዶችና 983 ሴቶች በድምሩ 33692 ሰዎች በመረጃ ማዕከሉ የተለያዩ መረጃዎች ተጠቃሚ ሆነዋል። ሴቶች በመረጃ ማዕከላት በብዛት ተጠቃሚ አለመሆናቸውን የተስተዋለ ሲሆን ወደፊት ትኩረት የሚያስፈልገው መሆኑን ያሳያል። በነዚህ መረጃ ማከላት 235 የሚሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተጠቃሚ ሆነዋል።

በበጀት ዓመቱ በማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ በተከናወኑ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ 3 ጋዜጣዊ መግለጫዎች የተሰጡ ሲሆን እነዚህም በራዲዮና በቴሌቭዥን ለህዝብ እንዲቀረቡ ተደርጓል። የተለያዩ የዶክመንቴሽን ስራዎችም ተከናዉነዋል።

### 1.2. የማህበረሰብ ውይይት

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር ረገድ ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተከናወኑ ከሚገኙ ተግባራት አንዱ የማህበረሰብ ውይይት ነው። የማህበረስብ ውይይት በአለፉት ጥቂት አመታት ተጨባጭ ለውጥ በማምጣት አመርቂ ውጤት  እንዲመዘገብ አስችሏል።

የማህበረሰብ ውይይት በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ በቀጥታም ሆነ በተዛዋዋሪ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ላይ በመወያየት ችግሩን በመለየት አካባቢያዊ መፍትሔ በማስቀመጥ በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በድጋፍና እንክብከቤ በአድልዎና

መገለል ወዘተ ዙሪያ ጥልቅና ተከታታይ የሆነ ውይይት በማካሄድና ልዩ ልዩ ዉሳኔዎችን በማሳለፍ የህብረተሰቡን አቅም እያጐለበተ ይገኛል፡፡

የማህበረሰብ ውይይት ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር በተጨማሪም ለድጋፍና እንክብካቤ እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ሲሆን ለአብነትም፡-

- ከዚህ በፊት ለኤች አይ ቪ መስፋፋት ምክንያት የነበሩ በርካታ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲቀንሱ አድርጓል፣
- ህብረተሰቡ በድጋፍና እንክብካቤ ተግባራት ጉልህ የሆነ ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል፣
- ህብረተሰቡን ያሳተፈ የፀረ ኤችአይቪ/ኤድስ ንቅናቄ እንዲፈጠር አድርጓል ፣
- ህብረተሰቡ እያገኘ ባለው ግንዛቤ የኤች አይ ቪ የደም ምርመራና ከእናት ወደ ልጅ የኤች አይ ቪ መተላለፍ በመከላከል እንዲሁም የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚነቱ እንዲጨምር አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡
- አድልዎና መገለል በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የማህበረሰብ ውይይት ፣ ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በገቢ ማስገኛ ተግባራት እንዲሳተፉ አይነተኛ መፍትሄ እየሆነ ይገኛል፡፡

የማህበረሰብ ውይይት የሚካሄድባቸው ቀበሌዎች ብዛት 3409 የጣቢያዎች ቁጥር ደግሞ 8876 የማህበረሰብና 3462 የትምህርት ቤት በድምሩ 12338 ደረሷል ፡፡ 807622 ያህል ተሳታፊዎች ውይይቱን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡ ቀጥታ ባልሆነ (በተዘዋዋሪ) የውይይት ተሳታፊዎቹ በቤተሰብና በአካባቢ አምስት ሰዎችን በመረጃ ልውውጥ ቢደርሱ 4038110 ያህል ህዝብ ተጠቃሚ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከውይይቱ ተሳታፊዎች 450072 *(60%)* ያህሉ ወንዶች ሲሆኑ 357550 *(40%)* ያህሉ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡

# የማህበረሰብ ውይይት አፈፃፀም ማጠቃለያ

| ተ. ቁ | ዞን | የማህበረ ሰብ ውይይት የሚካሄድ ባቸው ቀበሌዎች | አጠቃላይ የጣቢያዎች ብዛት | | | | የተካሄደ የውይይት ብዛት (Session | በማህበረሰብ ውይይት የተሳታፊዎች ብዛት/አማካይ/ | | | የት/ቤት ማህበረሰብ ውይይት የሚካሄድ ባቸው ት/ቤቶች ብዛት | የተካሄደ ውይይ ት ብዛት (Session) | በትም/ማህ/ውይይት የተሳታፊዎች ብዛት /አማካይ/ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ነባር /ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያልገቡ | አዲስ | ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የገቡ | ድምር | | ወንድ | ሴት | ድምር | | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ሰ/ሸዋ | 413 | 469 | 369 | 188 | 1026 | 5845 | 31491 | 20970 | 52461 | 414 | 2195 | 13144 | 13128 | 26272 |
| 2 | አዊ | 201 | 289 | 504 | 18 | 811 | 6763 | 34572 | 24822 | 59394 | 229 | 510 | 12059 | 9562 | 21621 |
| 3 | ኦሮሚያ | 113 | 4 | 113 | 112 | 229 | 2646 | 9385 | 6645 | 16030 | 150 | 1366 | 5240 | 5260 | 10500 |
| 4 | ምዕ/ጎጃም | 391 | 221 | 453 | 295 | 969 | 5130 | 33405 | 25776 | 59181 | 381 | 2431 | 15324 | 14834 | 30158 |
| 5 | ደ/ጎንደር | 325 | 164 | 189 | 275 | 628 | 8854 | 20961 | 18290 | 39251 | 337 | 4217 | 11097 | 10685 | 21782 |
| 6 | ምስ/ጎጃም | 424 | 132 | 614 | 1315 | 2061 | 34556 | 59079 | 37103 | 96182 | 528 | 5021 | 18144 | 15511 | 33655 |
| 7 | ሰ/ጎንደር | 571 | 202 | 422 | 459 | 1083 | 12861 | 46254 | 37264 | 83518 | 511 | 4560 | 25246 | 22604 | 47850 |
| 8 | ሰ/ወሎ | 278 | 25 | 295 | 223 | 543 | 2827 | 18609 | 16971 | 35580 | 299 | 1100 | 13281 | 10494 | 23775 |
| 9 | ደ/ወሎ | 547 | 112 | 356 | 623 | 1091 | 10071 | 44850 | 33806 | 78656 | 437 | 3116 | 17185 | 12771 | 29956 |
| 10 | ዋግኽምራ | 125 | 2 | 115 | 269 | 386 | 4847 | 13120 | 13260 | 26380 | 132 | 1979 | 4616 | 4784 | 9400 |
| 11 | ባ/ዳር | 21 | 42 | 0 | 7 | 49 | 422 | 1470 | 1470 | 2940 | 44 | 44 | 1540 | 1540 | 3080 |
| | ድምር | 3409 | 1662 | 3430 | 3784 | 8876 | 94822 | 313196 | 236377 | 549573 | 3462 | 26539 | 136876 | 121173 | 258049 |

## 1.3 የማህበረሰብ አቀፍ ኤድስ ፕሮግራም

ይህ ፕሮግራም ከማህበረሰብ ውይይት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ህብረተሰቡን የሚያሳትፍ ፕሮግራም ሲሆን በክልሉ ባሉት ሁሉም ወርዳዎች በተጠናከረ ሁኔታ እየተካሄደ ያለ ፕሮግራም ነዉ፡፡ በያዝነዉ በጀት አመት በዓመት ዉስጥ በአጠቃላይ 3287 ቀበሌዎች የተደረሱ ሲሆን ፤ በእነዚህ ቀበሌዎች 1880912 ቤተሰቦች ተደርሰዋል ፡፡ እራሱን ከወረርሽኙ በመከላከል ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግ ለሌሎች አከባቢዎች አርዓያ ሊሆን የሚችል የባለቤትነትና ሃላፊነት የሚፈጥር ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ዋና ዋና ተግባራትም ስልጠናዎች፣ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አሳታፊ የሆነ የምክክር ፕሮግራምና የተሻሉ ስራዎች የልምድ ልውውጥ የሚከሄድበትና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

**የበጎ ፈቃድ ፀረ-ኤድስ መልዕክተኞች ኘሮግራም ዕቅድ ክንውን /በቤተሰብ ደረጃ በኘሮግራሙ የተደረሱ ብዛት/**

| ተ.ቁ | ዞን | መለኪያ | የ2002 በጀት ዓመት ዓመታዊ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | | ክንውን | | | |
| | | | ቀበሌ | ቤተሰብ | ቀበሌ | % | ቤተሰብ | % |
| 1 | ሰ/ሸዋ | ቁጥር | 424 | 367200 | 373 | 87 | 223970 | 61 |
| 2 | አዊ | ቁጥር | 201 | 60300 | 201 | 100 | 47581 | 84 |
| 3 | ኦሮሚያ | ቁጥር | 113 | 36780 | 113 | 100 | 58430 | 158 |
| 4 | ምዕ/ጎጃም | ቁጥር | 395 | 282960 | 393 | 99 | 263816 | 100 |
| 5 | ደ/ጎንደር | ቁጥር | 335 | 181240 | 324 | 96 | 372562 | 208 |
| 6 | ምስ/ጎጃም | ቁጥር | 426 | 281351 | 390 | 91 | 262139 | 93 |
| 7 | ሰ/ጎንደር | ቁጥር | 577 | 266286 | 550 | 95 | 242174 | 91 |
| 8 | ሰ/ወሎ | ቁጥር | 309 | 81120 | 259 | 84 | 95339 | 117 |
| 9 | ደ/ወሎ | ቁጥር | 517 | 223893 | 550 | 106 | 189377 | 85 |
| 10 | ዋግኽምራ | ቁጥር | 125 | 33275 | 113 | 90 | 116974 | 351 |
| 11 | ባ/ዳር | ቁጥር | 21 | 6500 | 21 | 100 | 8550 | 131 |
| | ድምር | | 3443 | 1820171 | **3287** | **95** | **1880912** | **103** |

## 1.4 የኤች.አይ.ቪ. የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት

የኤችአይ ቪ. የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት የኤች.አይ.ቪ.ን ሥርጭት ባለበት ለመግታት ከኤች.አይ.ቪ. ነፃ የሆኑ ልጆች እንዲወለዱ በማድረግ ጤነኛ ቤተሰብ ለመመስረት የወደፊት ሕይወትን በዕቅድ ለመምራት የፀረ ኤች አይ ቪ. መድሃኒት ለመጠቀም የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምክንያት ለሚከሰቱ ተጓዳኝ በሽታዎች ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኙ ለማድረግ መግቢያ በር ነው።

በአሁኑ ወቅት በክልሉ 520 የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡ ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ቅስቀሳ የተደረገ ከመሆኑም በላይ በክልሉ የማህበረሰብ ውይይት እየተካሄደ በመሆኑና ከፍተኛ የሆነ የመመርመር ፍላጎት በመፈጠሩ ከመደበኛ የአገልግሎት መስጫዎች በተጨማሪ በተንቀሳቃሽ ጣቢያዎችም አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

በበጀት ዓመቱ ዉስጥ በሁሉም ዞኖች ለ 3,000,951 ሰዎች የኤች.አይ.ቪ. የምክርና ምርመራ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ3,120,732 ሰዎች አገልግሎቱ ተሰጥቷል። ይሄም ከዕቅዱ የ103% አፈፃፀም አለው ይህም ከባለፈዉ ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ1,474,899ተጠቃሚዎች ወይም የ47% ብልጫ አለዉ። በዚህ ሪፖርት መሠረት ከተመረመሩት 1700248 ወንዶች ውስጥ 20683*(1.2%)* እንዲሁም ከተመረመሩት 1420984 ሴቶች መካከል 28935 ***(2.04%)*** የሚሆኑት ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ተገኝቶባቸዋል በአጠቃለይ በዓመቱ ከተመረመሩት 3120732 ሰዎች ዉስጥ 49618 ያህሉ ኤች አይ ቪ. ተገኝቶባቸዋል። ከሪፖርቱ እንደምንገነዘበው ከተመረመሩት ውስጥ በቁጥር ወንዶቹ የሚበልጡ ቢሆንም ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው የተገኘባቸውን ስንመለከት ግን የሴቶቹ ቁጥር ከፍተኛ እንደሆነ ማየት ይቻላል። በመሆኑም በመከላከሉ በድጋፍ አሰጣጡ እንዲሁም በህክምናው በኩል ለሴቶች የተለየ ትኩረት የሚያስፈልግ መሆኑን ያረጋግጣል።

በአጠቃላይ በክልሉ የኤች አይ ቪ. የደም ምርመራ በህ/ሰቡ እየተለመደ መሆኑን፣ ህብረተሰቡም ከኤች.አይ.ቪ. ተጋላጭነት ራሱን የመጠበቅ ልምዱ መሻሻሉን እንዲሁም እየተካሄዱ ያሉት የመከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ውጤታማ እየሆኑ እንደመጡ ያመለክታል።

# የ2002 የምክርና የደም ምርመራ ዕቅድ አፈፃፀም

| ተ.ቁ | ዞን | ዓመታዊ እቅድ | VCT | | | | | | PIHCT | | | | | | HCT | | | ለህክምና ክትትል ሪፈር የተደረጉ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ ያደረጉ | | | ኤች አይ ቪ የተገኘባቸው | | | የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ ያደረጉ | | | ኤች አይ ቪ የተገኘባቸው | | | | | | | | |
| | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | ሰ/ሸዋ | 321649 | 175295 | 128818 | 304113 | 1245 | 1714 | 2959 | 13174 | 24997 | 38171 | 471 | 967 | 1438 | 188469 | 153815 | 342284 | 1076 | 1595 | 2671 |
| 2 | አዊ | 134746 | 72533 | 66150 | 138683 | 469 | 717 | 1186 | 8621 | 15518 | 24139 | 152 | 347 | 499 | 81154 | 81668 | 162822 | 522 | 953 | 1475 |
| 3 | ኦሮሚያ | 78897 | 56235 | 51197 | 107432 | 420 | 460 | 880 | 11286 | 12953 | 24239 | 179 | 302 | 481 | 67521 | 64150 | 131171 | 213 | 298 | 511 |
| 4 | ምዕ/ጎጃም | 443804 | 172769 | 115318 | 288087 | 867 | 1243 | 2110 | 23384 | 23406 | 46790 | 442 | 677 | 1119 | 196153 | 138724 | 334877 | 1175 | 1676 | 2851 |
| 5 | ደ/ጎንደር | 208038 | 126920 | 93351 | 220271 | 878 | 1104 | 1982 | 27301 | 32521 | 59822 | 481 | 727 | 1208 | 154221 | 125872 | 280093 | 618 | 947 | 1565 |
| 6 | ምስ/ጎጃም | 618236 | 206262 | 146704 | 352966 | 1700 | 2305 | 4005 | 51887 | 62495 | 114382 | 1251 | 2028 | 3279 | 258148 | 209199 | 467347 | 1768 | 2637 | 4405 |
| 7 | ሰ/ጎንደር | 281836 | 177153 | 144243 | 321396 | 2747 | 3613 | 6360 | 17676 | 20949 | 38625 | 1182 | 1289 | 2471 | 194829 | 165192 | 360021 | 800 | 948 | 1748 |
| 8 | ሰ/ወሎ | 416627 | 77704 | 67148 | 144852 | 1477 | 1721 | 3198 | 10651 | 15798 | 26449 | 664 | 916 | 1580 | 88355 | 82946 | 171301 | 1193 | 1260 | 2453 |
| 9 | ደ/ወሎ | 379066 | 360272 | 281092 | 641364 | 3608 | 5156 | 8764 | 37841 | 37264 | 75105 | 1050 | 1384 | 2434 | 398113 | 318356 | 716469 | 2384 | 3430 | 5814 |
| 10 | ዋግኽምራ | 104790 | 39253 | 35645 | 74898 | 196 | 279 | 475 | 4315 | 5124 | 9439 | 171 | 279 | 450 | 43568 | 40769 | 84337 | 82 | 119 | 201 |
| 11 | ባ/ዳር | 13262 | 24160 | 31536 | 55696 | 757 | 1222 | 1979 | 5557 | 8757 | 13914 | 276 | 485 | 761 | 29717 | 40293 | 70010 | 89 | 146 | 235 |
| | ድምር | 3000951 | 148556 | 1161202 | 2649758 | 14364 | 19534 | 33898 | 211693 | 259782 | 471075 | 6319 | 9401 | 15720 | 1700248 | 1420984 | 3120732 | 9920 | 14009 | 23929 |

## 1.5 ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል

የኤች.አይ.ቪን ሥርጭት ለመግታት ከፍተኛ ትኩረት ከተሠጣቸው ተግባራት መካከል አንዱ ከእናት ወደ ልጅ ኤች አይ ቪ እንዳይተላለፍ መከላከል ነው፡፡ ኤች.አይ.ቪ በደማቸው የተገኘ ባቸው ነፍሰጡር እናቶች ኤች.አይ.ቪ ወደ ህፃኑ እንዳይተላለፍ የሚያስችለውን ሕክምና እንዲያገኙ ግንዛቤ የመስጠትም ሆነ የአገልግሎቱ አቅርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜም እየተስፋፋ ይገኛ ል፡፡

በበጀት አመቱ ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ በ 316 የጤና ድርጅቶች አገልግሎቱን የማቅረብ ስራ እየተሰራ ሲሆን ለ 285593 እናቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 201291 ነፍሰ ጡር እናቶች ምርመራ በማድረግ ተጠቃሚ ሁነዋል፡፡ ክንውኑም የዕቅዱን 70.48% ነዉ፡፡ ክነዉኑ ከባለፈዉ በጀት ዓመት ጋተር ሲነፃፀር የ102753 ወይም የ51% ተጠቃሚዎች ብልጫ አለዉ፡፡ የኤች.አይ.ቪ የደም ምርመራ ካደረጉት ነፍሰጡር እናቶች *2.37%* ወይም 4790ዎቹ ኤች.አይ.ቪ በደማቸው የተገኘ ሲሆን 1959 እናቶችና 1455 ህፃናት ኤች.አይ.ቪ ወደ ህፃናት እንዳይተላለፍ የሚረዳ መድሀኒት አገልግሎት እንዲጠቀሙ ተደርገዋል፡፡ በተጨማሪ በተለያዩ ቦታዎች ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳተላለፍ 2110 የእናቶች ለእናቶች ድጋፍ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

# ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል እቅድ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | ዞን | ዓመታዊ ዕቅድ የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ ያደረጉ | ቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ያገኙ(ANC) | የምክር አገልግሎት ያገኙ | የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ ያደረጉ | ኤች አይ ቪ/በደማ ቸው የተገኘ | ARV prophylaxis እና በወሊድ ወቅት NVP የተጠቀሙ ድምር | በወሊድ ወቅት NVP የተሰጣቸ ው ህፃናት | Partner Tested የተመረመሩ አጋሮች | ኤች አይ ቪ የተገኘባቸ ው የትዳር አጋሮች | የተቋቋሙ MSG | ኤችአይ ቪ የተገኘባቸው በድጋፍ ቡድን /MSG/ የተካተቱ፣ እናቶች | የአልሚ ምግብ ተጠቃሚ የሆኑ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | ህፃናት | እናቶች |
| 1 | ሰ/ሸዋ | 16331 | 17902 | 16147 | 15624 | 293 | 108 | 103 | 2804 | 22 | 18 | 114 | 28 | 93 |
| 2 | አዊ | 14643 | 18426 | 19129 | 17314 | 130 | 80 | 65 | 4040 | 24 | 14 | 66 | 95 | 89 |
| 3 | ኦሮሚያ | 16000 | 12024 | 12024 | 12024 | 105 | 45 | 51 | 3318 | 08 | 6 | 43 | 8 | 28 |
| 4 | ምዕ/ጎጃም | 22742 | 17963 | 17915 | 17686 | 222 | 120 | 65 | 4213 | 29 | 18 | 209 | 2 | 36 |
| 5 | ደ/ጎንደር | 37813 | 22322 | 18807 | 15116 | 238 | 129 | 102 | 3555 | 26 | 11 | 293 | 54 | 57 |
| 6 | ምስ/ጎጃም | 49818 | 45445 | 44514 | 37911 | 681 | 335 | 147 | 3609 | 56 | 64 | 455 | 872 | 237 |
| 7 | ሰ/ጎንደር | 50391 | 32064 | 27908 | 24324 | 1335 | 350 | 269 | 4198 | 35 | 15 | 47 | 65 | 0 |
| 8 | ሰ/ወሎ | 19589 | 15936 | 16145 | 13844 | 577 | 208 | 146 | 1712 | 41 | 52 | 152 | 16 | 16 |
| 9 | ደ/ወሎ | 47125 | 32147 | 39344 | 40561 | 897 | 342 | 285 | 5795 | 118 | 23 | 334 | 146 | 109 |
| 10 | ዋግኽምራ | 9941 | 6170 | 4540 | 3015 | 73 | 30 | 10 | 257 | 0 | 8 | 48 | 131 | 608 |
| 11 | ባ/ዳር | 1200 | 7822 | 5997 | 3872 | 239 | 212 | 212 | 18 | 2 | 2 | 369 | 7 | 43 |
| | ድምር | 285593 | 228221 | 222470 | 201291 | 4790 | 1959 | 1455 | 33519 | 361 | 231 | 2130 | 1424 | 1316 |

## 1.6 የኮንዶም ትውውቅና ሥርጭት

ጥንቃቄ የጎደለው የግብረስጋ ግንኙነት ዋና የኤች አይ ቪ መተላለፊያ መንገድ ከመሆኑ አንፃር ኮንዶምን በአግባቡና ሁልጊዜ መጠቀም በተለይም ለወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ማቅረብ አንዱ ትኩረት የተሰጠው ተግባር ነው፡፡ ዲኬቲ ኢትዮጵያና የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ኮንዶምን በማስተዋወቅና በማሠራጨት በዋናነት የሚሰሩ ሲሆኑ በሌሎች አካላትም ማለትም በአይቴክ ኢትዮጵያ፣በፖፑላሽን ሰርቪስ ኢትዮጵያ፣በቤተሰብ መምሪያ፣ በአልማ፣ በፀረ ኤድስ ክበባት፣ በግል የጤና ድርጅቶች እንዲሁም በሱቆችና በመድሐኒት ቤቶች ስርጭቱ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በባጀት አመቱ  ዉስጥ ጤና ጥበቃን ጨምሮ በተለያዩ አካላት 28017352 ኮንዶሞች (36843481 የወንድና 868076 የሴት) ለማሠራጨት ታቅዶ 18864321 የወንድና 142867 የሴት ኮንዶም በድምሩ 19007188 ኮንደም ተሠራጭቷል፡፡ ከዕቅድ አንፃር አፈፃፀሙ የሚያሳየው በተለይ የሴት ኮንዶም ስርጭት ለወደፊቱ ትኩረት መስጠት የሚያስፈልገዉ መሆኑን ነዉ፡፡

# የኮንዶም ትውውቅና ሥርጭት

| ተ.ቁ | ዞን | በ2002 በጀት ዓመት የተሰራጨ የኮንዶም ብዛት /ዕቅድ/ክንውን/ — የወንድ | | | የሴት | | | ድምር | | | የኮንዶም ማስራጫ ጣብያዎች ብዛት | የኮንዶም አያያዝና አጠቃቀም ኮሚቴ ማቋቋም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | ክንውን | % | ዕቅድ | ክንውን | % | ዕቅድ | ክንውን | % | | |
| 1 | ሰ/ሸዋ | 4413814 | 2193275 | 49 | 2000 | 413 | 4 | 4415814 | 2193688 | 49 | 458 | 15 |
| 2 | አዊ | 2000000 | 328125 | 15 | 20000 | 1290 | 7 | 2020000 | 329415 | 16 | 188 | 31 |
| 3 | ኦሮሚያ | 520000 | 367776 | 95 | 57560 | 73 | 0.1 | 577560 | 367849 | 92 | 117 | 3 |
| 4 | ምዕ/ጎጃም | 4987286 | 1460511 | 28 | 15000 | 500 | 4 | 5002286 | 1461011 | 28 | 295 | 12 |
| 5 | ደ/ጎንደር | 928723 | 789860 | 85 | 175319 | 3361 | 5 | 1104042 | 793221 | 71 | 299 | 52 |
| 6 | ምስ/ጎጃም | 8912003 | 1792558 | 20 | 398964 | 103605 | 26 | 9310967 | 1896163 | 36 | 235 | 41 |
| 7 | ሰ/ጎንደር | 5287051 | 2063018 | 39 | 45886 | 23320 | 50 | 5332937 | 2086338 | 39 | 389 | 0 |
| 8 | ሰ/ወሎ | 351195 | 1834078 | 522 | 18484 | 0 | 0 | 369679 | 1834078 | 496 | 304 | 83 |
| 9 | ደ/ወሎ | 6961620 | 2078875 | 30 | 83304 | 721 | 5 | 7044924 | 2079596 | 29 | 323 | 33 |
| 10 | ዋግኽምራ | 1381789 | 487769 | 34 | 28516 | 0 | 0 | 1447005 | 487769 | 33 | 164 | 6 |
| 11 | ባ/ዳር | 1100000 | 1520616 | 138 | 23043 | 4584 | 26 | 1123043 | 1525200 | 136 | 37 | 20 |
| | ክልል | 0 | 3947860 | | 0 | 5000 | | 0 | 3952860 | | | |
| | ድምር | 36843481 | 18864321 | 51 | 868076 | 142867 | 16 | 37748257 | 19007188 | 50 | 2809 | 296 |

## 1.7 የአባላዘር በሽታዎችን መከላከልና ማከም

የአባላዘር በሽታ የኤች አይ ቪ/ኤድስን ስርጭት ከሚያባብሱት ከዋና ዋና ምክንያቶች መካከል አንዱ ሲሆን በአባለዘር በሽታዎች የተያዙ ሠዎች ለኤች.አይ.ቪ. ያላቸው ተጋላጭነት ከጤነኛ ሰዎች ጋር ሲነፃፀር የበለጠ በመሆኑ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግና የተጋለጡትን ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በበጀት አመቱ ዉስጥ ለ139177 ሰዎች የአባላዘር በሽታ ሕክምና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ 28377 ሰዎች አገልግሎቱ ተሰጧል፡፡ ክንውኑም የዕቅዱ 20.39% ነው፡፡

### የአባላዘር በሽታ ህክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛት ማጠቃለያ

| | ዞን | የ2002 በጀት ዓመት/ዓመታዊ/ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | | | ክንውን | | |
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድምር |
| 1 | ሰ/ሸዋ | 9360 | 8640 | 18000 | 833 | 1032 | 1865 |
| 2 | አዊ | 500 | 500 | 1000 | 457 | 538 | 995 |
| 3 | ኦሮሚያ | 1181 | 1189 | 2370 | 234 | 356 | 590 |
| 4 | ምዕ/ጎጃም | 14863 | 14870 | 29733 | 880 | 1158 | 2038 |
| 5 | ደ/ጎንደር | 2323 | 1514 | 3634 | 838 | 1066 | 1904 |
| 6 | ምስ/ጎጃም | 16239 | 15916 | 32155 | 1819 | 2684 | 4503 |
| 7 | ሰ/ጎንደር | 7399 | 8030 | 15441 | 2602 | 2810 | 5412 |
| 8 | ሰ/ወሎ | 3439 | 3325 | 6764 | 1177 | 1238 | 2415 |
| 9 | ደ/ወሎ | 11639 | 11094 | 26579 | 2789 | 3964 | 6753 |
| 10 | ዋግኽምራ | 1846 | 2031 | 3501 | 412 | 381 | 793 |
| 11 | ባ/ዳር | 4000 | 4000 | 8000 | 417 | 692 | 1109 |
| | ድምር | 68789 | 67109 | 139177 | 12458 | 15919 | 28377 |

## 1.8 በስራ ቦታዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መከላከል

የመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ልዩ ልዩ ተቋማት በስራ ቦታዎች ኤች.አይ.ቪን በመከላከል እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሠረት አበረታች ጅምሮች እየታዩ ነው፡፡ በሲቪል ሰርቪስና በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ የተዘጋጀውን የስራ ቦታዎች መመሪያ በማስተዋወቅና አፈፃፀም በመከታተል፣ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ያለባቸውን ሠራተኞች መብት ከማስጠበቅ አኳያ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ለአብነትም በባህር ደር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ለሚሰሩ የማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት የሰራተኛ ተወካይና ቫይረሱ በደማቸዉ የለባቸዉ ሰዎች ያካተተ ዉይይት ፤በኮምቦልቻ ከተማ ለሚገኙ ከ10 ኢንዱስትሪዎች ለተዉጣጡ የማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት የሰራተኛ ተወካይና ቫይረሱ በደማቸዉ የለባቸዉ ሰዎች ያካተተ ዉይይት በማካሄድ በየስራ ቦታቸዉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

### 1.9 ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የተከናወኑ ተግባራት

ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ለኤች አይ ቪ የተጋለጠ ቢሆንም ነገር ግን በስራ ባህሪያቸዉ በፆታና በዕድሜ የበለጠ ለኤች.አይ.ቪ የተጋለጡ አካላት ላይ ትኩረት በማድረግ በአነስተኛ ወጭ ጊዜና የሠዉ ሃይል በፍጥነት የተሻለ ውጤት ማምጣት የሚቻል በመሆኑ የተለየ ጥረት እንዲደረግ ይጠበቃል፡፡ ከእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎችም ወጣቶች፣ ሴቶች፣ መለዮ ለባሹ፣ ተንቀሳቃሽ ሠራተኞች፣ሹፌሮች እና መምህራን ይገኙበታል፡፡ ከላይ በተገለፁት ተግባራት ተጠቃሎ የቀረበ ቢሆንም ለነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች የተደረገውን ጥረት ለማሳየትና ወደፊትም አጠናክሮ ለመቀጠል እንደሚከተለው ተገልፆአል፡፡

- ወጣቱን ትኩረት ያደረጉ በፀረ ኤድስ ክበባት አማካኝነት በድራማ በስነ ጽሑፍ በሙዚቃ በመነባነብና በመሳሰሉት በመከላከሉ ዙሪያ በክልሉ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡
- በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ላሉ የፀረ ኤድስ ክበባትንና የመረጃ ማዕከላትን፣ ሚኒሚዲያዎችን በማkkምና በማጠናከር ወጣቱን ከኤች አይ ቪ እንዲከላከል እየተደረገ ነው፡፡ የአቻ ለአቻ ውይይቶች፤የወጣቶች ዉይይትና የህይወት ክህሎት ስልጠናዎች ወጣቶችን ማዕከል አድርገዉ እየተካሄዱ ናቸው፡፡

- ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል እንዲጠቀም የሚበረታታ ቢሆንም በተለይም ወጣቱ፣ሴተኛ አዳሪዎችና መለዮ ለባሹ የህብረተሰብ ክፍል ከዕድሜውና ከስራ ባህርይው አንፃር ኮንዶም እንዲጠቀም ይጠበቃል። ስለሆነም የኮንዶም አቅርቦት እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች በሚገኙባቸዉ ቦታዎች በስፋት እየተካሄደ ይገኛል። በባህር ዳር ከተማ ለ3716 ሴተኛ አዳሪዎች በኮንዶም ላይ ገለፃ ተደርጓል።
- የኤች.አይ.ቪ ስርጭት ከፍተኛ ደረጃ በደረሰባቸው የክልሉ የተመረጡ አካባቢዎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ትኩረት ያደረገ ጥናት ተጠናቋል። ጥናቱን መነሻ በማድረግም ከኤፍ.ኤች.አይ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር በተመረጡ 5 ወረዳወች የመከላከል ስራው ተጀምሯል።
- በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ በርካታ የመከላከልና ድጋፍ ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን በተለይም በሴተኛ አዳሪዎች ላይ ከተሰሩ ስራዎች ሁለገብ የመከላከል ስልጠና፣ የአቻ ለአቻ ትምህርት፣ የንግድ ክህሎት ስልጠናና የመነሻ ካፒታል መስጠት ይገኙበታል። ከዚህ በተጨማሪ ኤች.አይ.ቪ ላለባቸው ሴቶች በገቢ ማስገኛ እንዲሰማሩ ተደርጓል።በተለያዩ ዞኖች በሆቴል ተቀጥረው ለሚሰሩ፣የስልጠናና የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል።
- በክልሉ ከፍተኛ የሆነ የባህርይ ለውጥ እያመጣ ያለው የማህበረሰብ ውይይት ላይም ሴቶች ቢያንስ *50* በመቶ እንዲሆኑ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።
- በክልሉ ውስጥ በሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች(በመንገድ ስራ፣በመስኖ ልማት)፣በሰፈራ አካባቢ፣በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካባቢ የሚገኘውን ህብረተሰብና የፕሮጀክት ሠራተኞች ከኤች.አይ.ቪ ለመጠበቅ ትኩረት በመስጠት በርካት ስራዎች ተከናውነዋል።

በአጠቃላይ በመከላከሉ ዘርፍ ከላይ በተዘረዘሩት የትኩረት መስኮች በልዩ ልዩ አካላት በርካታ ሰራዎች የተከናወኑ ሲሆን በተቋም ደረጃ በስራ ቦታዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከል እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ በልዩ ልዩ መንገዶች ግንዛቤ ተፈጥሯል። እነዚህ ተግባራትም ከለጋሽ ድርጅቶችም ሆነ ከአካባቢው በተገኘ ሃብት ተከናውኗል።

## 2. ድጋፍና ክብካቤ

ድጋፍና እንክብካቤ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ውስጥ ጉልህ ድርሻ ይሰጠዋል፡፡ ስለሆነም በክልላችን ኤች አይ ቪ በደማቸው ለሚገኝባቸውና ለኤድስ ህሙማን እንዲሁም ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ልጆች በበርካታ ፈፃሚ አካላትና ማህበራት በኩል ድጋፍና ክብካቤ እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል፡፡

### *2.1. ኤች አይ ቪ በደማቸው ለሚገኝባቸውና ለኤድስ ህሙማን ድጋፍና የማህበራት እንቅስቃሴ*

በ2002 በጀት አመት በድምሩ ለ *242134* ኤች አይ ቪ በደማቸው ለሚገኝና ኤድስ ህሙማን ድጋፍና ክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ 144217 ሰዎች  በተለያዩ የድጋፍ አይነቶቸ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ክንውኑም 60%  ሲሆን ፧21 ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ላለባቸው ሰዎች ከክልል ቢሮዎች በkሚነት በየወሩ የሚደገፉ ይገኙበታል፡፡ የተሰጡ የድጋፍ አይነቶችና የተጠቃሚዎች ብዛት  እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

በክልሉ በአጠቃላይ 150 የሚሆኑ ኤች.አይ.ቪ በደማቸዉ የተገኝባቸዉ ሰዎች ማህበራት ተደራጅተው አባሎቻቸው በተለያዩ የገቢ ማስገኛ የድጋፍና ክብካቤ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልም የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር እንዲሁም በሌሎች ተግባራት እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡

ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ያለባቸዉ ሰዎች ማህበራት አባላት የተሰማሩባቸዉ የገቢ ማስገኛ ተግባራት ዋና ዋናዎቹ፡-

- የከብት፣ በግ፣ ፍየል እና ዶሮ እርባታና ማድለብ
- ንብ ማነብ
- በሰብል ምርትና በጓሮ አትክትልት ልማት
- ሸቀጣሸቀጥ ንግድ
- ወፍጮ ቤት
- በሆቴል አገልግሎት
- በካፍቴሪያ አገልግሎት
- በጽህፈት መሳሪያዎችና ሱቅ
- የፎቶ ኮፒ ስራ
- አሸዋ፣ ቡሎኬትና ሌሎች የግንባታ ቁሳቁሶች ማምረት
- ወዘተ--- ይገኙበታል

ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው የተገኘባቸው ወገኖች የድጋፍና እንክብከቤ አገልግሎት እቅድ አፈጻጸም

| ድጋፍና ክብንቤ አገልግሎት የስራ ዝርዝር | መለኪያ | የ2002 በጀት ዓመት/ዓመታዊ/ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | | | ክንዉን | | | |
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ንጽጽር |
| የስነ ልቦና የምክር አገልግሎት ማህበራዊ ድጋፍ | የተደገፉ | 37702 | 44286 | 81888 | 24650 | 33275 | 57925 | 70 |
| የምግብ ድጋፍ | የተደገፉ | 18463 | 24915 | 40875 | 10148 | 15895 | 26043 | 64 |
| የመጠለያ ድጋፍ | የተደገፉ | 8002 | 9933 | 17935 | 543 | 1059 | 1602 | 9 |
| በገቢ ማሰገኛ ተግባራት ስልጠና መስጠት | የተደገፉ | 15888 | 20411 | 36199 | 3843 | 7569 | 11412 | 32 |
| ለገቢ ማስገኛ ተግባራት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ | የተደገፉ | 16773 | 20916 | 37599 | 4496 | 8272 | 12768 | 34 |
| የቤት ለቤት ድጋፍና ክብካቤ ያገኙ | | 12726 | 14912 | 27638 | 13546 | 20921 | 34467 | 124 |
| ድምር | | ***109554*** | ***135373*** | ***242134*** | 57226 | 86991 | 144217 | 60 |

## *2.2. ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ልጆች የሚደረግ ድጋፍ*

ወላጆቻቸውን በኤድስና በሌሎች ምክንያቶች የሚያጡ ተጋላጭ ልጆች ቁጥር ከሚደረገው የድጋፍና ክብካቤ ምላሽ በላይ በመሆኑ በርካታ ልጆች ለጎዳና ህይወትና ሌሎች ችግሮች እየተጋለጡ ይገኛሉ፡፡ የነዚህ ልጆች ችግሮች ዘላቂታዊ መፍትሄ የሚሹ ቢሆኑም በክልላችን የሚገኙ አጋር ድርጅቶችና ፈፃሚ አካላት ከተለያዩ ምንጮች በሚገኘውና በአካባቢው ሃብት የገንዘብ ድጋፍ ለጥቂቶቹ የመሠረታዊ ፍላጐትና የትምህርት ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

- ✓ በበጀት ዓመቱ 265503*(87%)* ወላጆቻቸውን ያጡና ተጋላጭ ልጆች የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ይህም ከ2001 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ 126522 ወይም የ47% ብልጫ አለዉ፡፡

